# ለመሆኑ ክርስቲያኖቹ ይህንን ያዉቃሉን?

1 እግዚአብሔር፡ የጻፈለችሁንም ስርዓትና ፍርድ ህግና ትዕዛዝም ለዘለዓለም ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ፤ ሌሎችንም አማልክት አትፍሩ። 2ኛ ነገስት 17፡37
2 እግዚአብሔር የስምንት ቀን ልጅ ይገረዝ በቤት የተወለደ ወይም ከዘራችሁ ያይደለ በብርም ከእንግዳ ሰዉ የተገዛ ወንድ ሁሉ በትውልዳችሁ ይገረዝ በቤትህ የተወለደ በብርም የተገዛ ፈጽሞ ይገረዝ ቃል ኪዳኔም በስጋችሁ የዘለዓለም ቃል ኪዳን ይሆናል የቁልፈቱን ስጋ ያልተገረዘ ቁላፍ ሰዉ ሁሉ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና። ኦሪት ዘፍጥረት 17፡12-14
3 ኢየሱስ፡ እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትዕዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰዉም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰዉ በመንግስተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል። ማቲዎስ 5፡19
4 ጳዉሎስ ከእግዚአብሔርና ከኢየሱስ ይበልጣልን? ምን ያህልስ ደፋር ነዉ?
ህጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትዕዛዝ ተሽራለች። ዕብራውያን 7፡18-19
5 ጳዉሎስ፡ እነሆ እኔ ጳዉሎስ እለችኃለሁ ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም በህግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋዉ ወድቃችኃል። ገላቲያስ 5፡1-6
እላይ በ2 እና በ 3 ቁጥር ከተጠቀሱት ጋር የሚጋጭ ትምህርት ጳዉሎስ ከማን ተምሮ ነዉ የሚያስተምረዉ? እግዚአብሔርና ኢየሱስ ያላስተማሩትን?
6 ጳዉሎስ፡ ሰዉ ያለ ህግ ስራ በዕምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና። ሮሜ 3፡28 እላይ በ3 ቁጥር የተጠቀሰዉንና ቀጥሎ በ7 ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉን ስናገናዝብ ጳዉሎስ ምን አይነት ሰዉ እንደ ሆነ መረዳት ይቻላል።
7 ትዕዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነዉ እናዉቃለን አውቄዋለዉ የሚል ትዕዛዛቱንም የማይጠብቅ ዉሸተኛ ነዉ እዉነትም በርሱ ዉስጥ የለም። 1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 2፡3-4
አንተ ከንቱ ሰዉ እምነት ከስራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታዉቅ ትወዳለህን? የያዕቆብ መልዕክት 2፡20 ሁለቱ ሐዋሪያት ዮሐንስና ያዕቆብ የጳዉሎስ አይነት ትምህርት የሚያስተምር ሰዉ ከንቱና ዉሸተኛ ነዉ ይላሉ።
8 ጳዉሎስ በራሱ ላይ እንደሚከተለዉ ሲመሰክር ተመልከቱ፡- ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነትን እንዳልታበይ የሥጋዬ መዉግያ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልዕክተኛ ተሰጠኝ። ይኸዉም እንዳልታበይ ነዉ። 2ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 ምናልባት ከንቱ እና ዉሸተኛ የሚያሰኝ ሥራ የሰራዉ በተሰጠዉ የሰይጣን መልዕክተኛ ይሆን ይሁን?
9 ጳዉሎስ፡ ስለድንግልም የጌታ ትዕዛዝ፡ የለኝም ነገር ግን የታመንሁ እሆን ዘንድ ከጌታ ምህረት የተቀበልሁ እንደምሆኔ ምክር እመክራለሁ። 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡25 ጳዉሎስ፡ ከ12 ሐዋሪያት ዉጭ ሆኖ እንዴት ሆኖ የታመነ ሊሆን ይችላል ዮሐንስና ያዕቆብ ዉሸተኛ እና ከንቱ እያሉት? ይባስ ኢየሱስ በመንግስተ ሰማያት ታናሽ ነዉ ብሎታል በማቴዎስ 5፡19 ህግን በመሻር ለሰዉ የሚያስተምር በመጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ ማንም ሰዉ የለም ከጳዉሎስ በስተቀር። በስም ጠቅሰዉ ጳዉሎስ አላለዉም እንጂ ማቴዎስ 5፡19 እርሱን፡ ይመለከታል።
ሥራ የሌለዉ ዕምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነዉ። የያዕቆብ መልዕክት 2፡17
10 ጳዉሎስ አንድ ቀን ወደ ደማስቆ እየሄደ እያለ ብርሃን መጣበት እና
1ኛ ሁላችን ወደቅን የሐዋሪያት ሥራ 26፡9-20
2ኛ ጳዉሎስ ብቻዉን ወድቆ ሌሎች ቆመው ድምፅ ሰሙ እንጂ ብርሃኑን አላዩም የሐዋ ሥራ 9፡1-9
3ኛ ከርሱ ጋር የነበሩት ሰዎች ብርሃኑን አዩ እንጂ ድምጹን አልሰሙም። የሐዋ ሥራ 22፡6-11

# በመጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ ኢየሱስ ብቻ ነዉ ጌታ የተባለዉ?

1. አብረሃም፡ ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሏል። ኦሪት ዘፍጥረት 18፡12
2. ኤልያስ፡ አብድዩም በመንገድ ሲሄድ እነሆ ኤልያስ ተገናኘዉ። አብድዩም አወቀዉ በግንባሩም ተደፍቶ ጌታዬ ሆይ ኤልያስ አንተ ነህን? አለ። 1ኛ ነገስት 18፡7
3. ኤልሳዕ፡ የከተማይቱም ሰዎች ኤልሳዕ እነሆ ጌታችን እንደምታይ የዚህች ከተማ ኑሮ መልካም ነዉ ዉሃዉ ግን ክፉ ነዉ ምድሪቱም ፍሬዋን ትጨነግፋለች አሉት። 2ኛ ነገስት 2፡19
4.ሙሴ፡ አሮንም፡- ጌታዬ ሆይ ቁጣህ አይቃጠል፤ይህ ህዝብ ክፋትን እንዲወድ አንተ ታዉቃለህ። ኦሪት ዘፀአት 32፡22
5. ዮሴፍ፡ እነርሱም አሉት ጌታችን ሆይ አይደለም ባርያዎችህ ስንዴን ሊገዙ መጥተዋል። ኦሪት ዘፍጥረት 42፡10

ስለዚህ ጌታ የተባሉት ሰዎች ሁሉ አምላክ ከሆኑ ስንት አምላኮች አሉ? በመጻህፍ ቅዱስ ዉስጥ ኢየሱስም ጌታ ነዉ የተባለዉ እንጂ አምላክ አልተባለም ጌታና አምላክ አንድ አይደሉም ።

የሚከተለዉ የመጽሀፍ ቅዱስ አንቀጽ ጌታና አምላክን ለይቶ ያስተምራል።

ለኛስ ነገር ሁሉ ከርሱ የሆነ እኛም ለርሱ የሆነን አንድ አምላክ አብ አለን። ነገር ሁሉ በርሱ በኩል የሆነ እኛም በርሱ በኩል የሆነን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። 1ኛ ቆሮ 8፡6 መንፈስ ቅዱስስ ተረሳ?

በመጨረሻም ለክርስቲያኖች የቤት ሥራ የሚሆኑትን ጥያቄዎች እንጠይቃለን።

አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሰራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ። ኤፌሶን 4፡5-6

1. አንድ ሃይማኖት የትኛዉ ነዉ? ኦርቶዶክስ? ፕሮቴስታንት? ወይንስ ካቶሊክ?
2. ኢየሱስ፡ ጌታ ነዉ ወይንስ፡ አምላክ?

‹‹ሐዋሪያቶቹ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።›› የሐዋ ሥራ 11፡26

1. የኢየሱስና የሐዋሪየቶች ኃይማኖት ኢየሱስ በሚያስተምርበት ወቅቶች ምን ነበር? ምክንያቱም ኢየሱስ፡ ወደ ሰማይ ከወጣ በኃላ ነዉ ሐዋሪያቶቹ ክርስቲያን ተብለዉ የተሰየሙት።

ኢየሱስ ጌታ የሚሆነዉ፡ ወደ ሰማይ ስለወጣ ነዉ ለሚሉት፡ መልሱ ሄኖክም ወደ ሰማይ ወጣ ኦሪት ዘፍጥረት 5፡24 ኤልያስም በአዉሎ ንፋስ፡ ወደ፡ ሰማይ ወጣ 2ኛ ነገስት 2፡11

ሌላዉ ምክንያት ደግሞ ሙታን ስላነሳ ነዉ፡ ጌታ የሚሆነዉ፡ ለሚሉት መልሱ ኤልያስ የሞተዉን ሰዉ ቀስቅሷል። 1ኛ ነገስት 17፡22  ኤልሳዕ በ2ኛ ነገስት፡ 4፡34 የሞተዉን ሰዉ አስነስቷል። ስለዚህ ወደ ሰማይ መዉጣት እና ሙታንን መቀስቀስ ጌታ የሚያሰኝ ከሆነ ሄኖክ ኤልያስና ኤልሳዕም ጌቶች ናቸዉ ማለት ነዉ?

ክርስቲያኖች ኢየሱስ ፍጹም፡ ሰዉ ፍጹም አምላክ ነዉ ይላሉ ይህም በ451 በቀልኪዳን ጉባኤ የተደነገገ እንጂ በምንም፡ መልኩ፡ እግዚአብሔር ሰዉ እንደማይሆን መጽሀፍ ቅዱስ ያስተምራል።

ሀሰት ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰዉ አይደለም ይጸጸትም ዘንድ እግዚአብሔር የሰዉ ልጅ አይደለም ኦሪት ዘኍልቅ 23፡19

ሠ. የርህራሄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። 2ኛ ቆሮ 1፡3

‹‹ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ።›› ዮሐንስ 20፡17 ይህም ማለት እግዚአብሔር የሁሉም አባትና አምላክ እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ብቻ አይደለም። የመልክቱ መደምደምያ ግን ኢየሱስ አምላክ እንዳልሆነ እና የራሱ አምላክ ግን እንዳለዉ ዓለም እንዲገነዘብ ነዉ።